ጥናታዊ ዘገባ በማቅረብ የሕዝቡን ጽምዕ ለአለም ሕብረተሰብ በማሰማት የዘረኛውን ወያኔ ገበና በማጋለጥ ላይ የሚገ" የሲዳማን ትግል ለማስተባበርና ለመምራት በሀገር ውስጥና በውጭ በሰፋ ሕዝባዊ ድጋፍ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት ነው።

**የሲዳማ ድርጅቶች ወቅታዊ እንቅስቃሴ ሲገመገም**

በተለያዩ ሁኔታዎች ለጊዜው በትግል ሂደት ውስጥ እንዳሉ በይፋ የሚታወቁት ከላይ የተጠቀሱት 3 ድርጅቶች ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በሲዳማ ምድር የተቀጣጠለው የተማሪዎችና ሕዝባዊ ፀረ ወያኔ ተቃውሞ ከደረሰበት ደረጃ አንፃር 3ቱም ድርጅቶች ሕዝባዊ ትግሉን በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ ከማስተባበርና ከመምራት አንፃር ከፍተኛ የሆነ ድክመት ይታይባቸዋል። የድክመታቸውም አቢይ ምክንያት ለጋራ አላማ መሳካት ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በጋራ ግንባር በአንድነት ያለመንቀሳቀሳቸው ይሆናል። ድርጅቶቹ በአንድነት እንድሰሩ በሀገር ውስጥና በውጭ ያለ እያንዳንዱ የሲዳማ ዜጋ ምኞቱ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ምክር በመለገስና ጫና በመፍጠር ላይ ይገኛል። አንድነትን እስካላመጡ ድረስ ጫናው ወደፊትም ቀጣይ ይሆናል።

**መታወቅ ያለበት እዉነታ**

ስለእያንዳንዱ ድርጅት ጥንካሬና ድክመት ስናነሳ መገንዘብ የሚገባን እውነታ አለ። 3ቱም ድርጅቶች የየራሳቸውን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያሉ ቢሆንም ለሚያደርጉት የትግል እንቅስቃሴ የሚያገኙት ውስጣዊና ውጫዊ ድጋፍና እገዛ ወሳ"ነት አለው፡ ከ3ቱ ድርጅቶች ላለፉት አምስትና ስድስት አመታት ከተለያዩ የትግል አጋር ድርጅቶችና ወገኖች የማቴሪያል; የፋይናንሻልና የሎጀስቲክ ድጋፎች በማግኘት በመንቀሳቀስና እውቅና በማግኘት SLF ብቸኛ ድርጅት ሲሆን ሁለቱ ግን በተለይም SNLO ምንም ውጫዊ ድጋፍ ሳይኖረው በአባላቱ ተሳትፎ ብቻ የሚንቀሳቀስ ነው። ስለሆነም የ3ቱን ድርጅቶች እንቅስቃሴ ሲንገመግም ይህንን እውነታ ከግንዛቤ ውስጥ እያስገባን መሆን አለበት።

**በጋራ ለመንቀሳቀስ የተደረጉ ተግባራዊ ጥረቶች**

ከላይ እንደተመለከተው የሲዳማን ትግል ውጤታማ ለማድረግ በጋራ መሥራቱ ወቅታዊና አማራጭ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ በSNLO አነሳሽነትና ጋባዥነት ድርጅቶቹን በተለይም በውጭ እየተንቀሳቀሱ ያሉትን ለማቀራረብ ካለፉት ሶስትና አራት ወራት ጀምሮ ቀላል የማይባል ሥራ እየተሰራ ነው። በርካታ ውይይቶች ተደርገዋል። በእርግጥ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ የሁሉም ግለሰብ ወይም ቡድን ሚናና አስተዋጽኦ ቀና ነበር ማለት ያስቸግራል። የተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ከግል ጥቅም ይሁን ወይም ከሲዳማ ሕዝብ መብት ከማስከበር አንፃር መለየት በሚያስቸግር ሁኔታ ከጅምሩ እስካሁን ድረስ አፍራሽና ከፋፋይ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ያሉ ቢሆንም ያንን በመቋቋምና በማክሸፍ በጋራ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል የመንገዱን አስቸጋሪውን ክፍልና አብዛኛውን ርቀት መሸፈን ተችሎ ነበር።ለአላማው መሳካት በርካታዎቹ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ምክራቸው በመለገስ ሂደቱን በጥሞና ሲከታተሉ ነበር። ይህ ሁሉ ሆኖ መጨረሻው እንደተጠበቀው ያለመጠናቀቁን በከፍተኛ ሀዜንና የውርደት ስሜት ለማሳወቅ ብንገደድም መንገዱ ጨርሶ እንዳልተዘጋና ጥረቱ ቀጣይነት እንደሚኖረው በማረጋገጥም ጭምር ነው።

**በዉይይቱ ወቅት ሲያጋጥሙ የነበሩ እንቅፋቶች**

1ኛ/ ባለፈው ውይይት ከስምምነት ላይ የተደረሱ ነጥቦችን መሻር ወይም መካድና በሚቀጥለው ውይይት በአዲስ መልክ ወይም በተቃራኒው ማንሳት
2ኛ/ አለመተማመንና ከፋፋይና አፍራሽ አሉባልታዎችን ማናፈስ
3ኛ/ በሚረባና በማይረባ ምክንያት ጊዜ ማባከን
4ኛ/ ሁሉም የሲዳማ ዜጋ በትግሉ እንዳይሳተፍ በቡድንና በጎሰ"ነት መከፋፈል
5ኛ/ ለአንድነቱም ሆነ ለትግሉ በቁርጠ "ነት ያለመነሳት
6ኛ/ ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ ለግል ጥቅምና አላማ ማሳካት ቅድሚያ መስጠት ይሆናሉ።

**ከስምምንት ተደርስዉ የነበሩ ነጥቦች**

በውይይቱ ወቅት ከላይ የተመለከቱ አፍራሽ ሂደቶችን በማክሸፍ በውጭ ሀገር ያሉ የSLF ና የSNLO ድርጅቶች ቀጥሎ የተዘረዘሩ ነጥቦች ላይ ከስምምነት ደርሰው ነበር።

እዚህ ላይ ማሳወቅ የሚንሻው ጉዳይ ከላይ እንደተጠቀሰው በውይይቱ ቀጥታ የተሳተፉት SLF እና SNLO ቢሆኑም በውጭ ያሉ በተለይም የSLM ቀደምት ታጋዮችና የነፃነት ፋና ወጊዎችና እንዲሁም በሀገር ውስጥ ያሉ አመራርና አባላት በአንድነት ለመስራት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸውና ለዚህም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ እንደነበር ማስገንዘብ እንሻለን።

1ኛ/ ሁለቱ ድርጅቶች ተጨፍልቀው አንድ እንድሆኑ

እንደሚታወቀው የተለያዩ ድርጅቶች በተለያዩ መንገዶች አንድ ላይ ለመንቀሳቀስ ይስማማሉ። ድርጅቶቹ የነበራቸውን ስምና አላማ አንድ አድርገው ውህደት መፍጠር(Unity) ወይም ስማቸውንና አላማቸውን እንደያዙ